3) ከተሳሳተ አመለካከታቸው እንዲታረሙ ቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ ትችላለች?

4) ከኖኅ የስካር ታሪክ ውስጥ ለመሪዎች ማስጠንቀቂያ የሚሆነው ምንድነው?

5. ጸሎት።

ትምህርት አምስት

ዘፍጥረት 10-11፥ ክለሳ

አንደኛ ቀን፡- ዘፍ. 10

1ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ከኢትዮጵያ ውስጥ የአሥር ጎሳዎችን ስም ዘርዝር።

ለ) የጎሳ ክፍፍል የሚታየው ልምንድነው?

ሐ) ከእነዚህ ክፍፍሎች የሚመነጩ ችግሮች ምንዳናቸው?

የምንኖርባትን ዓለም ስንመለከት፥ ዓለም በተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ተከፋፍላ እናያለን። በሺህ የሚቆጠሩ ቋንቋዎችና በሺህ የሚቆጠሩ የተለያዩ የሕዝብ ቡድኖች ይስተዋላሉ። ይህም አንዱ ቡድን ሌላውን ወደሚዋጋበት ጎሰኝነት አምርቷል። ይህ የሆነው ለምንድነው? የጎሳዎችና የቋንቋዎች መከፋፈል የተጀመረው የት ነበር? ዘፍጥረት 10 ና 11 የዓለምን የመከፋፈል ምስጢር ይገልጹልናል። በዘፍጥረት 10፥ ሙሴ የተለያዩ የዓለም ነገዶች እንዴት ሦስት ልጆች ከነበሩት ከአንዱ ኖኅ እንደመጡ ያሳያል። የጥቁር ሕዝቦች አባት የሆነው የካም ልጆች፥ የአውሮፓውያንና የእስያውያን አባት የሆነው የያፌት ልጆችና የአይሁዶችና የዐረቦች አባት የሆነው የሴም ልጆች ናቸው።

ዳሩ ግን ዛሬ ዓለም ምንም ያህል በጎሳና በዘር ሐረጎች ብትከፋፈልም፥ በሰው ልጆች መካከል የአንድነትን ስሜት ሊጭር የሚገባው ባሕርይ አለ። አስቀድመን ይህንን አንድነት ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል ከመፈጠራቸው አኳያ ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ይህንን አንድነት የሰው ልጆች ሁሉ ከአንዱ የኖኅ ቤተሰብ ከመምጣታቸው አኳያ እንመለከታለን። ጳውሎስ ለአቴና አሕዛቦች

እንደጻፈው «ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ፥ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፤ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ሥፍራ ዳርቻ መደበላቸው። ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም» (የሐዋ. 17፡26-27)።

2ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ጳውሎስ በሰው ልጆች መከፋፈልና በሚኖሩበት ሥፍራ ረገድ እግዚአብሔር ስለነበረው ድርሻ ምን ይላል?

ለ) እንደ ጳውሎስ አገላለጽ፥ እግዚአብሔር ይህንን ያደረገው ለምን ነበር?

3ኛ ጥያቄ፤ ዘፍ. 10-11 አንብብ። ለሰው ልጆች መከፋፈል ምክንያት ሆነው የተሰጡት ሁለት አበይት ነገሮች ምንድናቸው?

4ኛ ጥያቄ፤ ዘፍ. 10ን አንብብ ሀ) ሦስቱ አበይት የሰው ዘር ቤተሰቦች እነማን ናቸው?

ለ) ከመጽሐፉ በስተ ጀርባ ያለውን ካርታ ተመልከት። እያንዳንዱ ዋና ዋና ቤተሰብ የመጣው ከየት ነበር?

ሐ) በእዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተዘረዘሩት ሕዝቦች ወይም ነገዶች ስንት ናቸው?

መ) ኢትዮጵያውያን ከየትኛው ነገድ የተገኙ ናቸው?

ሠ) ይህ ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔርና ሰው የሚያስተምረን ምንድነው?

እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን በፈጠረ ጊዜ፥ የሰጣቸው የመጀመሪያው ትዕዛዝ ምድርን እንዲሞሉዋት ነበር። ዳሩ ግን አዳምና ሔዋን እንዲሁም ልጆቻቸው ይህን ትዕዛዝ ባሚሉ መጠን፥ ኃጢአትም እየበዛ እንደ መጣ ተመልክተናል። ክፋት እጅግ ሰለ በዛ፥ ከኖኅና ቤተሰቡ በስተቀር፥ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ አጠፋ። በእግዚአብሔር ጸጋና ኖኅም ለእግዚአብሔር የታዛዥነትን ሕይወት ስለኖረ፥ ከጥፋቱ ውኃ አመለጠ።

ከጥፋት ውኃ በኋላ፥ እግዚአብሔር ምድርን በዘራቸው እንዲሞሏት ለኖኅና ቤተሰቡ ወዲያውኑ ዳግም ትዕዛዝ ሰጠ። ዘፍጥረት 10 ይህ እንዴት እንደ ተፈጸመ ይገልጻል። የኖኅን ሦስት ልጆችና አንዳንድ ትውልዶቻቸውን ያሳያል። በዚህ ክፍል የኖኅ ልጆች ትውልዶች በሙሉና የዓለም ሕዝቦች ሁሉ አልተጠቀሱም።

ሙሴ ዘፍጥረት 10ን ሲጽፍ አራት አበይት ዓላማዎች ነበሩት፡-

ሀ. የሰው ዘር እንዴት አንድነት እንዳለው ለማሳየት ይፈልጋል። ሁሉም ሰው የመጣው ከአንዱ ሰው፥ ኖኅ ነው። ስለሆነም የሰው ልጅ በሙሉ የአንድ ቤተሰብ አካል ነው።

5ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ይህ ከእኛ ነገድ ወይም ዘር አንድ ካልሆኑት ሰዎች ጋር የሚኖረንን ግንኙነት እንዴት ሊለውጠው ይገባል?

ለ) በደቡብ አፍሪካ ስለሰፈነው የዘር መድልዎስ (አፓርታይድ) ይህ ምላሽ የሚሆነው እንዴት ነው?

የትም ሥፍራ ብንኖር፥ ከየትኛውም ነገድ ብንሆን፥ ሁላችንም ከአንድ ምንጭ መጥተናል። ሁላችንም የአዳም ልጆች ነን፤ እንዲሁም ደግሞ የኖኅ ልጆች ነን። ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን፥ በታሪካቸው ሁሉ ጠላቶች ሆነው በቆዩት ሰዎች መካከል የተሻለ ግንኙነት ለመሻት ይህንን እውነት መሠረት አድርገን ልንጠቀምበት ይገባል። ሰይጣን ከምድር ላይ ሰላምን ለማጥፋት እነዚህን ልዩነቶች ለመጠቀም ይፈልጋል።

እነዚህ በሰዎችና በባሕሎች መካከል የሚገኙ ልዩነቶች፥ የእግዚአብሔርን የመፍጠር ችሎታ የሚያንጸባርቁ ሆነው ሊታዩ ይችላሉ። እግዚአብሔር አንድ ዓይነት ዛፍ ወይም ተክል ብቻ እንዳልሠራ ሁሉ፥ እንዲሁ ደግሞ ሰዎች በተለያየ ሁኔታ እንዲኖሩ ፈቅዷል። አንዱ ነገድ ወይም የሕዝብ ቡድን ከሌላው በላይ አይደለም። ወይም የበለጠ የእግዚአብሔር አምሳል የለውም። «ያልሰለጠኑ ወይም ያልተማሩ» ሰዎች እንደ እንስሳት ናቸው ለማለት አንችልም። ሁሉም ባሕሎችና የሕዝብ ቡድኖች በከፊል የእግዚአብሔርን አምሳል ያንጸባርቃሉ። ባሕሎች ሁሉ በውስጣቸው አንዳንድ በጎና አንዳንድ

ክፉ ነገሮች አሏቸው። ሌሎችን የበታች አድርጎ ለመመልከት የሚያበቃ የዘረኝነት ትዕቢት የሚገኝበት ምንም ምክንያት የለም።

ኖኅና ሦስት ልጆቹ ምን ዓይነት የቆዳ ቀለም ነበራቸው? እኛ የምናውቀው ነገር ካለመኖሩም በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ ከብደት የተሰጠው ነገር አይደለም። አዳምና ሔዋን ወይም ኖኅ ምን ዓይነት የቆዳ ቀለም እንደ ነበራቸው አናውቅም። ሙሴ ከሦስቱ የኖኅ ልጆች በተገኙት የተለያዩ ነገዶች ላይ ትኩረት ቢያደርግም፥ ምን ዓይነት ቀለም እንደነበራቸው አልጠቀሰም። ጥቁሮች ከነጮች የበታች የሆኑ የሰው ዝርያዎች እንደሆኑ የሚቀርበውን የሐሰት ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ አይደግፈውም።

የተለያዩ የዘር ቡድኖች ከአንዱ ሰው እንዴት እንደ ጀመሩ አናውቅም። ምናልባት እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን በፈጠረ ጊዜ፥ የተለያዩ የሰው ቀለማት የመፍጠር ብቃት የያዙ ባሕርያት ይኖሩዋቸው ይሆናል። ይህም በእግዚአብሔር እቅድ መሠረት፥ የተለያዩ የዘር ቡድኖች እስከተገኙበት ጊዜ ድረስ የማይሠራ ሆኖ ቆይቷል። መሥራት የጀመረው ከጥፋት ውኃ በኋላ ነው። በሰሜኑ ወይም በደቡቡ ንፍቀ-ክበብ ውስጥ መኖር ከቆዳ ቀለማት ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚያረጋግጥ እውነተኛ መረጃም የለም።

ከሁሉም የሚልቀው ነገር፥ ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ መረዳቱ ሳይሆን፥ ሁላችንም ከአንድ ሰው እንደ መጣን የሚናገረው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው። ስለሆነም የአንድ ቤተሰብ አባላት ነን። ኅሰኝነት፥ በዘር መኩራራትና የበላይነትን ማሳየት፥ ዘረኝነት፥ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ስሕተት ናቸው።

6ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ኅሰኝነትና በዘር መኩራራት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው?

ለ) በቤተ ክርስቲያንስ ውስጥ እንዴት ይታያል?

ሐ) ኅሰኝነትን ለማስወገድ ቤተ ክርስቲያንህ ምን እያደረገች ነው?

መ) ሰዎች ፈካ ባለ ቆዳ ላይ ያን ያህል የሚያተኩሩት ለምንድነው? ይህ መልካም ነውን?

ለ. ምንም እንኳ የሰው ልጅ የአንድ ቤተሰብ አካል ቢሆንም፥ በከፍተኛ ደረጃ ተከፋፍሏል። ሙሴ ይህ ክፍፍል እንዴት እንደመጣ ለማሳየት ይፈልጋል። በአንድ በኩል፥ ሰዎች በዓለም ሁሉ በቤተሰብ ቡድን ውስጥ የሚኖሩትን ልጆች በመውለዳቸው፥ ብሔራዊ ክፍፍል የዚህ ዕድገት ውጤትና በተፈጥሮ የተከሰተ ሆኖ እናገኘዋለን። በነገው ትምህርታችን የነገድና የቋንቋ ክፍፍሎች ለምን እንደሚኖሩ የሚያስረዳውን ሌላ ምክንያት እንመለከታለን።

በእዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስማቸው የተዘረዘረ 70 የተለያዩ ነገዶች አሉ። በዚህም ምክንያት፥ አይሁዶች ዓለምን በ70 የተለያዩ የነገድ ቡድኖች እንደተከፋፈለች አድርገው ወስደዋታል። ከዚያም በመነሣት፥ በአዲስ ኪዳን ዘመን የዳስ በዓል ወቅት፥ አይሁዶች ስለ አሕዛብ 70 መሥዋዕቶችን ለእግዚአብሔር ይሠዉ ነበር።

ሙሴ ግን የዓለምን ሕዝቦች በሙሉ ለመዘርዘር አልሞከረም ነበር። አንዳንድ የኖኅ የልጅ ልጆች ብቻ ተጠቅሰዋል። ሙሴ ትኩረት የሰጠው በእስራኤል ሕዝብ አጠገብ ለነበሩት ነገዶች ነው። ስለሆነም ሙሴ በእስያ፥ በማዕከላዊና በደቡብ አፍሪካ፥ ወዘተ. ስለነበሩት ሕዝቦች ሳይሆን፥ በሜድትራኒያን ባሕር አካባቢ የነበሩት ሕዝቦች እንዴት እንደጀመሩ ብቻ ይናገራል።

ሐ. እንዲሁም ሙሴ እግዚአብሔር በሕዝቦች ሁሉ ላይ እንዴት የበላይ ተቆጣጣሪ እንደሆነም ለማሳየት ፍላጎት ነበረው። ሁሉም በእርሱ ጥበቃ ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን፥ ለሚኖሩበት ለየትኛውም ሥፍራ ሁሉ እርሱ ሙሉ መብት አለው። ስለሆነም፥ የከነዓንን ምድር ለተመረጠው ሕዝቡ ለእስራኤል የመስጠትና ከነዓናውያንን የማጥፋት መብት ነበረው።

መ. ከዚህም በተጨማሪ ሙሴ ለእስራኤላውያን በእግዚአብሔር የሚገዛው የአንዱ ዓለም አካል መሆናቸውን የማሳየትም ፍላጎት ነበረው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የተለዩ

ሕዝቦች እንዲሆኑለት ቢመርጣቸውም፥ ሁሉም ሕዝቦች ከአንዱ የኖኅ ቤተሰብ ስለ መጡ፥ እስራኤል እግዚአብሔርን በተመለከተ ለሌሎችም ሕዝቦች እውነትን የማስተላለፍ ሃላፊነት ነበረባት።

7ኛ ጥያቄ፤ ይህ ከቤተ ክርስቲያን ጥሪ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ሙሴ የዘር ሐረጎችን ፈር ያስያዘበትን ስልት መረዳቱ በጣም አስፈላጊ ነው። በዘፍጥረት ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ የትውልድ ሐረጎች ብናጠና፥ ጸሐፊው አብዛኛዎቹን በሁለት አኃዞች ዙሪያ እንደሚያደራጅ እንመለከታለን። በመጀመሪያ፥ ብዙዎቹ በ7 ቁጥር ዙሪያ ተደራጅተዋል። (ለምሳሌ የያፌትን 7 ልጆችና፥ 7 የልጅ ልጆች መመልከት ይቻላል)። ለአይሁዶች 7 ቁጥር የፍጹምነት ተምሳሌት ነበር። በሌሎች ጊዜያት ደግሞ ሙሴ የዘር ሐረጎቹን በ10 ቁጥር ዙሪያ አደራጅቷል። (ለምሳሌ ከአዳም እስከ ኖኅ፥ ከኖኅ እስከ አብርሃም አስር አስር የትውልድ ሐረጎች ተዘርዝረዋል)።

1. የያፌት የዘር ሐረግ (ቁ. 2-5)

የሚከተለው የነጭ ሕዝቦችና የእስያውያን አባት የሆነው፥ የያፌት ትውልድ ዝርዝር ነው፡-

...SPIRITUALITY / BROOKS FOUNDATION, INC.
...GREENVILLE AVE. ST. 810
...ON, TEXAS 75081, USA

ያፌት ፥

ጋሜር፥ ማጎግ፥ ማዴ፥ ያዋን፥ ቶቤል፥ ሞሳሕ፥ ቴራስ፥

አስከናዝ፥ ሪፋት፥ቴርጋማ፥ ኤሊሳ፥ ተርሴስ፥ ኪቲም፥ ሮድኢ

ምንም እንኳ እነዚህ የያፌት ልጆች ስሞች ቢሆኑም፥ በተጨማሪም በሙሴ ዘመን የነገዶችና የቦታዎች ስም ሆነው የሚታወቁ ነበሩ። ከእነዚህ ነገዶች ውስጥ አንዳንዶቹ የሚታወቁ ሲሆኑ፥ ሌሎቹ ግን ከእይታችን የራቁ ናቸው። የያፌት ትውልዶች ከእስራኤል በስተ ሰሜን፥ በሰሜን ምሥራቅና ሰሜን ምዕራብ ይገኛሉ። አንዳንዶቹ በትንሹ እስያ (በዛሬዋ ቱርክ)፥ በሰሜን ሩስያ ሲሆኑ፥ በብዛት ግን በአውሮፓ፥ በሜድትራንያን ባሕር ዳርቻና በባሕሩ ደሴቶች ውስጥ ይኖሩ ነበር። ምናልባት ፍልስጢኤማውያን ከዚህ የዘር ሐረግ ውስጥ ሊሆኑ ይችላሉ። (የጥንቶቹን ፍልስጥኤማውያን ከዛሬዎች ጋር ማምታታት አይገባም።

ምንም እንኳ በአግርኛ ስማቸው አንድ ቢሆንም፥ አንድ ሕዝብ አይደሉም)።

ነጮችና ምናልባትም እስያውያን የመጡት ከዚህ ሐረግ ነው።

8ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ከመጽሐፉ በስተጀርባ ያለውን ካርታ በመመልከት፥ ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ የት እንደሚገኙ አመልክት።

ለ) እነዚህ ሕዝቦች የኖሩባቸውን አገሮች ዘመናዊ ስሞች ተናገር።

2. የካም የዘር ሐረግ (ቁ. 6-20)

የሚከተለው የአፍሪካውያን አባት የሆነው የካም ትውልዶች ዝርዝር ነው፡-

ካም

ኩሽ ምድራይም ፉጥ ከነዓን

ሳባ ኤውላጥ ሰብታ ራዕማ ሰበቃታ ናምሩድ

ሳባ ድዳን

ምድራይም

ሉዲም ዓናሚም ላህቢም ንፍታሌም ፈትሩሲም ከስሉሂም ቀፍቶሪም

ከነዓን

ሲዶን ኬጢያውያን ኢያቡሳውያን አሞራውያን ጌርጌሳውያን ኤዊውያን ዑሩኪዎን ሲኒን አራዴዎን ሰማሪዎን አማቲን

9ኛ ጥያቄ፤ ከመጽሐፉ በስተጀርባ ያለውን ካርታ ተመልከትና ከእነዚህ ነገዶች መካከል እነዳንዶቹ የት እንደሚገኙ አመልክት።

ሙሴ ከያፌት ትውልዶች ይበልጥ በካም ትውልዶች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሲያደርግ እንመለከታለን። ይህም የሆነበት ምክንያት፥ ከእስራኤል በብዙ ሺህ ኪሎሜትር በሚቆጠር ርቀት ከኖሩት ያፌታውያን ይልቅ፥ የካም ትውልዶች በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወቱ ነው። የያፌት ትውልዶች እስከ ፋርስና

ሜዶን መንግሥት 539 ዓ.ዓ. ድረስ፥ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሚና አልነበራቸውም። ከእነርሱም በመቀጠል የያፌት ትውልዶች የነበሩት ግሪኮችና በኋላም ሮማውያን ተነስተው ነበር።

ሙሴ ኩሽ፥ ምጽራይና ከነዓን በተባሉት ሦስቱ የካም ልጆች ላይ ያተኩራል። ብዙዎቹ የካም ትውልዶች ከእስያ በስተ ደቡብ ምሥራቅና ከአፍሪካ በስተ ሰሜን ምሥራቅ በኩል ይገኙ ነበር። ለምሳሌ አንዳንድ ጊዜ ኢትዮጵያ ተብሎ የተተረጎመው ኩሽ በአሁኑ ጊዜ በደቡብ ግብፅ፥ በሰሜን ሱዳንና ምናልባትም በሰሜን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ክልል ነው። ሰባቱ የኩሽ ሕዝቦች በሙሉ በዐረብ ምድር ውስጥ ነበሩ (የዛሬዎቹ ሳውዲ ዐረቢያ፥ የመን፥ ወዘተ.)።

ሙሴ ከኩሽ ትውልዶች መካከል ናምሩድ ለተባለው ሰው የተለየ ትኩረት ይሰጣል። በርካታ ሊቃውንት ያነሱት ጥያቄ «ናምሩድ ማነው?» የሚል ነው። በእርግጠኝነት አናውቀውም። ዳሩ ግን ሙሴ በዚህ ምዕራፍ ካሉት ሰዎች ሁሉ በላይ ይህንን ሰው ይገልጸዋል። አንዳንዶች ሰዎች እንደሚያስቡት ናምሩድ ሌሎች ኩሻውያን ሕዝቦች ከኖሩበት ክልል ውጭ መኖሩ ስለ ተጠቀሰ፥ ይህ ሰው ከቁጥር 6-7 ውስጥ የተጠቀሰው የኩሽ ዘር አልነበረም ይላሉ። በኋላም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚገኘው፥ የናምሩድ ምድር ለአሦር ሕዝብ የተሰጠ ስም ነበር (ሚክ. 5:6)።

በጥንቱ ዓለም ናምሩድ በሁለት ነገሮች ይታወቅ ነበር። በመጀመሪያ፥ ኃያል አዳኝ በመሆኑ ይታወቅ ነበር። ምንም እንኳ ይህ እንስሳት የማዳን ችሎታውን ሊያመለክት ቢችልም፥ በይበልጥ ግን ሌሎች ሕዝቦችን የማሸነፍ ኃይሉን የሚገልጽ ነው - ኃያል ጦረኛ ነበር። ሙሴ «በእግዚአብሔር ፊት ኃያል አዳኝ» ብሎታል። ይህ ማለት ናምሩድ ድል ይነሣ ዘንድ በእግዚአብሔር የተመረጠና ኃይልን የተሞላ ነበር ማለት ነው። ጥንካሬውን ከእግዚአብሔር ተቀበለው እንጂ ከራሱ አለነበረም። ናምሩድ እንደመልካም ወይም እንደ ክፉ ሰው ሊታይ ይችላል። እንደ ክፉ ሰው አድርገው የሚያዩት ሰዎች፥ ናምሩድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በእግዚአብሔር ላይ እንዳመፀ ሰው ሆኖ ተገልጸአል ይላሉ። የባቢሎን ገንቢ እንደመሆኑ በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ በተሠራው የባቢሎን ግንብና ከተማ ግንባታ መሳተፍ

እንዳልነበረበት ይናገራሉ። ናምሩድን መልካም ሰው እንደሆነ የሚቆጥሩት ደግሞ፥ ለማሸነፍ የሚያስችል ኃይል የሚመጣው ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው አለመሆኑን ለማሳየት፥ በእግዚአብሔር ፊት ኃያል አዳኝ ተብሎ ተጠርቷል ይላሉ። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከባቢሎን ምርኮኛነት ለማውጣት ከአሕዛብ ወገን የነበረውን የሚዶን ንጉሥ ቂሮስን መሣሪያ አድርጎ እንደተጠቀመ ሁሉ (ኢሳ. 45፡1፥13 ተመልከት)፥ ናምሩድንም ዓላማውን በምድር ላይ ለማሳካት ተጠቅሞበታል።

10ኛ ጥያቄ፤- ዛሬ እግዚአብሔር በኃያላን ሰዎች (መሪዎች፥ አስተማሪዎች፥ የጦር ጄኔራሎች) እንደሚጠቀምና እንደሚቆጣጠር ለመናገር የምንችልበት መንገድ ምንድነው?

ናምሩድ በሜሶፖታሚያ አካባቢ በቆረቆራቸው በርካታ ከተሞችም ይታወቅ ነበር። ከእነዚህ ከተሞች ብዙዎቹ በኋላ ትላልቅና በጥንቱ ዓለም የታወቁ ሆነዋል። ሰባቱ ከተሞች፡- ሀ) ባቢሎን - በኋላ የባቢሎናውያን መንግሥት ዋና ከተማ ስትሆን፥ (በዚህና በምዕራፍ 11 ስናያር ተብላለች)።

ለ) ኦሬክ - በሰማርያ መንግሥት ታላቋ ከተማ።

ሐ) አርካድ - በሰሜናዊ የባቢሎን ግዛት ውስጥ የምትገኝ ሌላዋ ትልቅ ከተማ።

መ) ካልኔ - በሰሜን ሶሪያ ውስጥ የምትገኝ ከተማ።

ሠ) አሴር - የቀድሞዋ የአሦር መንግሥት ዋና ከተማ።

ረ) ነነዌ - የአሦር መንግሥት ዋና ከተማ የሆነችና ሰሜናዊ እስራኤልን የወረረች (722 ዓ.ዓ.)።

ሰ) በዛሬ ጊዜ የማይታወቁት ረሆቦት - ኢር፥ ካለህ፥ እና ሬሴን የሚባሉ ከተሞች ናቸው።

ምጽራይም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለግብፅ የተሰጠ ስም ነው። ከተጠቀሱት የምጽራይም ልጆች አብዛኞቹ በግብጽ አካባቢ ወይም

በዙሪያዋ በሚገኙ አገሮች (ለምሳሌ ሊብያ፥ ሱዳን፥ ኢትዮጵያ፥ ወዘተ.) ውስጥ ኑረዋል።

ፉጥ ዛሬ ሊብያ ተብላ ለምትታወቅ አገር የተሰጠ ስም ነው። ስለዚህ ትውልድ ምንም የተጠቀሰ ነገር የለም።

ሙሴ 11 የከነዓን ልጆች በመዘርዘር ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል። ይህም የሆነበት ምክንያት፥ እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር በሚሄዱበት ጊዜ የከነዓንን ትውልዶች ማጥፋት ስለነበረባቸው ነው። የመጀመሪያዎቹ የእስራኤል ሕዝብ ጠላቶች ከነዓናውያን ነበሩ። ሙሴ የከነዓናውያንን ድንበር በደቡብ ሊባኖስ ከሚገኘው ሲዶን እስከ ደቡብ እስራኤል ጌራራ (በአሁኑ የጋዛ ሰርጥ)፥ ከዚያም የሙት ባሕር ደቡባዊ ክፍል እስከ ሆኑት ሰዶምና ገሞራ ድረስ ያካልለዋል። ይህ ሁሉ ከነዓን በኢያሱ ከተያዘች በኋላ፥ የእስራኤል ሕዝብ ድንበር መሆን ነበረበት።

3. የሴም የዘር ሐረግ (ቁ. 21-32)

ለሙሴ ከኖኅ ትውልዶች ሁሉ እጅግ አስፈላጊዎቹ ሴማውያን ነበሩ። ይህም የሆነበት ምክንያት አብርሃምና በኋላም እስራኤላውያን የወጡት ከዚህ የሴም ሐረግ ስለነበረ ነው። ለዚህ ነው ሴማውያን በመጨረሻ ላይ የተጠቀሱት። እንዲሁም ሙሴ ‹በዔቦር ልጆች› ላይ አትኩሯል። አይሁዳውያን የመጡት በኋላ ዕብራውያን ተብለው ከተጠሩት ከዔቦር ትውልድ ነው።

ሴም

ኤላም አሦር አርፋክስድ ሉድ አራም

ቃይንም

ሳላ ዑፅ ሁል ጌቴር ሞሶሕ

ዔቦር

ፋሌቅ ዮቅጣን

ኤልሞዳድ ሣሌፍ ሐስረሞት ያራሕ ሀዶራም አውዛል ደቅላ ዖባል አቢማኤል ሳብ አፊር ኤውላጥ ዮባብ

የሴም ትውልዶች በሰፊ ክልል ውስጥ ተሰራጭተው ነበር። በስተ ምሥራቅ እስከ ፋርስ (ኢራን)፥ በስተ ደቡብ እስከ ኢትዮጵያና እስከ ደቡብ ዐረቢያ፥ በስተ ሰሜን አናቶሊያ (ቱርክ) እና በምዕራብ እስከ ቀርጤስ የክሬይት ደሴት ድረስ ኖረዋል።

ሙሴ ለተወሰኑ የሴም ትውልዶች የተለየ ትኩረት ይሰጣል። ሴማውያን አሁን በዓለም ዙሪያ በሴማዊነታቸው ይታወቃሉ። በመጀመሪያ የሚያተኩረው፥ በኋላ ወደ ዕብራውያን የተለወጡት የዔቦራውያን አባት በሆነው በዔቦር ላይ ነው። በዔቦር ሁለት ልጆች ላይም ትኩረት ተደርጓል። ዓለም የተከፋፈለችው የስሙ ትርጓሜ «ክፍፍል» በሆነው በፋሌቅ ዘመን ነበር። ይህ እግዚአብሔር ቋንቋቸውን በመደባለቅ በዓለም ውስጥ መከፋፈልን ለጀመረበት ለምዕራፍ 11 ታሪክ ማጣቀሻ ነው፤ የፋሌቅ ትውልዶች በምዕራፍ 11 ተጠቅሰዋል። የፋሌቅ ወንድም የዮቅጣን ትውልዶችም ተዘርዝረዋል።

የዓለም ቤተሰቦች ሁሉ የመጡት ከሦስት ሰዎች፥ ማለትም ከሴም፥ ከካምና ከያፌት ነው። በኖኅ የትውልድ ዝርዝር ውስጥ፥ እያንዳንዱ ተወላጅ እንደሕዝቡ ወይም ነገዱ አለቃ ሆኖ ተጠቅሷል። እነዚሁ ስያሜዎች ደግሞ የተለያዩ የቋንቋ ቡድኖችንም ይወክላሉ። ሙሴ እንዳለው «በየነገዳቸውና በየቋንቋቸው፥ በየምድራቸውና በየሕዛብቸው» ተለይተው ነበር (10፡20፥31)።

ዛሬም እንኳን የቋንቋ ሊቃውንት የቋንቋ ቡድኖችን ከተለያዩት የኖኅ ልጆች አንጻር ይዘረዝራሉ የሴማውያን ቋንቋዎች (ዕብራይስጥ፥ ዐረብኛ፥ አማርኛ፥ ጉራግኛ፥ ትግርኛ፥ ወዘተ.)፥ የካማውያን፥ የኩሻውያን ቋንቋዎች (ጌዴዎኛ፥ አሪ፥ ማሊ፥ ወዘተ.) እና ከያፌት የተወሰዱት እንግሊዝኛ፥ ፈረንሳይኛ፥ ወዘተ. ናቸው። ኢትዮጵያ የሁለቱ ዋና ዋና የቋንቋ ቡድኖች መገናኛ ስፍራ በመሆኗ ልዩ ነች። ብዙዎቹ የሰሜን ቋንቋዎች የሴማውያን ዓይነት ሲሆኑ፥ የደቡቦቹ ደግሞ እንደቀረው አፍሪካና ደቡብ ሰሃራ በካማውያን ቋንቋ ቡድን ውስጥ ይጠቃለላሉ።

11ኛ ጥያቄ፤- ከዚህ የሕዝቦች ዝርዝር ውስጥ፥ እግዚአብሔር በሕዝቦች፥ በቋንቋዎች፥ ወዘተ. ላይ ስላለው ቁጥጥር የምንማራቸውን አንዳንድ ትምህርቶች ዘርዝር።

እግዚአብሔር የሰዎች ሁሉ አምላክ ነው። ስለ አንድ አገር ወይም የሕዝብ ቡድን ብቻ የሚያስብ አይደለም። ይልቁንም ከሁሉም አገር ለሆኑት ሰዎች ሁሉ ይገደዋል። ለዚህ ነው ኢየሱስ በመጨረሻው ትዕዛዙ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱ ያዘዛቸው። ያ ትዕዛዝ ገና ከፍጻሜ አልደረሰም። ከመካከላቸው አንድም ሰው እንኳ በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምንባቸው አገሮችና ሕዝቦች አሁንም አሉ። ሁላችንም ወንጌሉን ይዘን ወደ ዓለም ሁሉ እንድንሄድ ታዘናል። ግን ይህን ትዕዛዝ እየፈጸምነው ይሆንን?

12ኛ ጥያቄ፤- ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ጎሳዎች ዘርዝር።

ለ) አማኞች የሌሉባቸውና ብዙ አማኞች ያሉባቸው የትኞቹ ጎሳዎች ናቸው?

ሐ) ቤተ ክርስቲያንህ ከሌላ ጎሳና ቋንቋ ለሆኑት ሕዝቦች ወንጌሉን ለማድረስ ያላት መሻት እንዴት ነው?

መ) በኢትዮጵያ ውስጥ ደኅንነት ላላገኙና ለጠፉት ሰዎች ወንጌሉን ለማድረስ፥ ቤተ ክርስቲያንህ የበለጠ መሥራት የምትችለው እንዴት ነው?

ሠ) በሌሎች አገሮች ውስጥ ደኅንነት ያላገኙትን ሰዎች ለመድረስ፥ ቤተ ክርቲያንህ መሥራት የምትችለው እንዴት ነው?

የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ አንድ ቀን ከየብሔረሰቡ ሁሉ ሰዎች በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እንደሚቆሙ ያሳያል። ራእይ 7፡9-10 እንዲህ ይላል፡- «ከዚህ በኋላ አየሁ፤ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊ በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤ በታላቅም ድምፅ እየጮኹ፡- በዙፋኑ

ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ።» እኛም ከእነዚህ እጅግ ብዙ ሰዎች ጋር በዙፋኑ ፊት ስለምንገናኝ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባል። ደግሞም እነርሱም በዙፋኑ ፊት ከእኛ ጋር አብረው እንዲገኙ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሁሉ በወንጌል ለመድረስ የተነቃቃ ጥረት ልናደርግ ይገባል።

ሁለተኛ ቀን፡- ዘፍጥረት 11፡1-9

ዛሬ ከተማርሃቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መመሪያዎች ውስጥ አንዳንዶቹን ከግብር ላይ ለማዋል ዕድል ይኖርሃል። ስለዚህም ወደ ትምህርት አንድ ተመልሰህ፥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚያመራውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ስልትና አበይት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መመሪያዎችን ከልስ። ማንኛውንም የትርጓሜ መጽሐፍ ሳትጠቀም፥ የሚከተለውን የቤት ሥራ አከናውን።

1. የምንባብ ክፍሉን ዋና አሳብ በአእምሮህ ለመቅረጽ ትችል ዘንድ፥ ዘፍ. 11፡1-9ን ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ በማስተዋል አንብብ። የክፍሉን ዋና ትምህርት በአንድ አጭር ዓረፍተ ነገር አጠቃልል።

2. ዘፍ. 11፡1-9 ደግመህ አንብብ። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ መመለስ ከሚገባን የመጀመሪያው ጥያቄ፥ ማለትም «መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?» ከሚለው ጋር የሚያያዙ ቢያንስ 10 ጥያቄዎችን አውጣ። ጥያቄዎቹን ካወጣህ በኋላ፥ አጫጭር መልሶችን ጻፍላቸው።

3. ዘፍ. 11፡19 እንደገና አንብብ። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ለምንጠይቀው ሁለተኛ ጥያቄ፥ ማለትም «መጽሐፍ ቅዱስ ምን ማለቱ ነው?» ለሚለው ምላሽ የሚሹ 5 ጥያቄዎችን አውጣ። ምናልባት ግልጽ ያልሆኑና የበለጠ ማባራራትን የሚጠይቁ የተወሰኑ ቃላት፥ ሐረጎች፥ ወይም አሳቦች ሊኖሩ ይችላሉ። ጥያቄዎቹን ካወጣህ በኋላ፥ መልሶቻቸውን ጻፍ። ለመተርጎም የሚያዳግቱ አንዳንድ ቃላት ቢያጋጥሙህ፥ መልሳቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ፈልግ።

4. ከዘፍ. 11፡1-9 ጥናትህ፥ «ይህ ለእኔ ወይም ለቤተ ክርስቲያን ምን ማለት ነው?» ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሹ ሦስት ጥያቄዎችን አውጣ። ከዚያም ይህ በግል ከራስህና ከቤተ ክርስቲያንህ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ አሳብ ስጥ።

5. በመጨረሻም፥ «ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ምን ማድረግ አለብኝ?» ለሚለው ጥያቄ ጥቂት መልሶችን ስጥ።

ወደ ነገው ትምህርት ከመሄድህ በፊት ይህንን ስለማጠናቀቅህ እርግጠኛ ሁን። እነዚህን ፍሬ ነገሮች በሳምንታዊ ስብሰባ ላይ ለሌሎች ስለምታካፍላቸው፥ ወደ ስብሰባው ይዘሃቸው ና። የእነዚህ ዓይነት ጥያቄዎችን አንዳንድ ምሳሌዎች በነገው ትምህርት ውስጥ ታገኛለህ። ያንተ ጥያቄ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከምትመለከተው ሊመሳሰል ወይም ሊለያይ ይችላል። ሁላችንም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተለያዩ ነገሮችን ስለምንመለከት፥ ለዚህ መጨነቅ አያስፈልግም።

ሦስተኛ ቀን፡- ዘፍጥረት 11

ዛሬ ዓይናችንን አቅንተን ዓለምን ስንመለከት፥ ዓለም የተስፋ ጭላንጭል በማይታይበት ሁኔታ ተከፋፍላ፥ ተበታትናና የሚኖርባትም የሰው ልጅ እርስ በእርሱ ተከፋፍሎ እናያለን። ይህ በሰው ልጆች መካከል የሚስተዋለው መከፋፈል የት ተጀመረ? የዓለም ሕዝብ እንዴት ከሦስቱ ዋና ዋና ሰዎች ካም፥ ሴምና ያፌት እንደ ተከፋፈለ ተመልክተናል። በዓለም የሚታወቁ የተለያዩ ጎሳዎችና ዘሮች ከእነርሱ የመጡ ናቸው። ዛሬ በሕዝቦች መካከል ይህ ትልቅ መከፋፈል ለምን እንዳስፈለገ እንመለከታለን።

13ኛ ጥያቄ፤ ዘፍጥረት 11ን አንብብ።

ሀ) ሰዎቹ ምን ለማድረግ አቀዱ?

ለ) ይህ የሆነው የት ነው?

ሐ) ሰዎቹ ይህን ለማድረግ የፈለጉት ለምንድነው?

መ) እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የፈረደው ለምንድነው?

ሠ) ፍርዱ ምን ነበር?

ረ) በሴም የዘር ሐረግ ውስጥ የነበሩትን ሰዎች ዘርዝር።

ሰ) በታራ የዘር ሐረግ ውስጥ የነበሩትን ሰዎች ዘርዝር። እርስ በእርሳቸው የተዛመዱት እንዴት ነው?

ሸ) ታራ በመጀመሪያ የኖረው የት ነበር? ከዚያስ ወዴት ሄደ?

በዘፍጥረት ጥናታችን፡ ሙሴ ለእስራኤላውያንና ለእኛም አስፈላጊ እውነቶችን ለማስተማር እንዴት የተወሰኑ ታሪኮችን እንደመረጠ በተደጋጋሚ ተመልክተናል። ሙሴ ለእስራኤላውያን ለማሳወቅ የፈለገው የዓለም ሕዝቦች በሙሉ ከየት እንደመጡ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የሰው ትዕቢትና ዝናን ፍለጋ መሯሯጥ፥ በእግዚአብሔር ላይ ወደማመፅ እንደሚያመራም ጭምር ለማሳየት ነበረ። ዛሬ በዓለማችን የሚታየው ችግር ይህ ነው።

14ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ትዕቢት ወይም ዝናን ፍለጋ መሯሯጥ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የሚያስከትላቸው አንዳንድ ችግሮች ምንድናቸው?

ለ) እነዚህ ነገሮች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የጎሳ ግንኙነቶች ላይ ችግር የፈጠሩት እንዴት ነው?

አንዳንድ ምሳሌዎችን ጥቀስ።

ዘፍጥረት 11 በሦስት ክፍሎች ሊከፈል ይችላል፡-

1. የባቢሎን ግንብ ግንባታ (ቁ. 1-9)

በዘፍጥረት 10፥ ሙሴ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ እንዴት ከተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ሐረጎች እንደ መጡ አሳይቷል። የሕዝቦች መከፋፈልና መበታተን እግዚአብሔር ለኖኅ እንዲባዙና ምድርን እንዲሞሉ የሰጠው ትዕዛዝ ፍጻሜ ነበር። እንዲሁም ዘፍ. 11፡1-9 የሕዝቦችን መበታተን ያሳያል። ዳሩ ግን በዚህ ሥፍራ ለመበታተን ምክንያት የሆነው፥ በሰው ዓመፀኛነትና ትዕቢት ላይ እግዚአብሔር የሰጠው ቀጥተኛ ፍርድ ነው። ከድርጊቶች ቅደም-ተከተል አንጻር፥ ዘፍጥረት 10 በምዕራፍ 11 የተዘገበውን የሕዝቦች መበታተን ተከትሎ የሚመጣ ነው።

ሙሴ የሰው ልጆች በአንድነት ወደ ነበሩበት ዘመን የኋሊት ይወስደናል። የሰው ልጅ በአንድነት ይኖርና አንድም ቋንቋ ይናገር ነበር። ያ ቋንቋ ምን እንደነበረ አናውቅም። ምናልባት ዛሬ ከሚነገሩት ቋንቋዎች ውስጥ የትኛውም ላይሆን ይችላል። መርከቧ ያረፈችበትን የአራራት ተራራ በመልቀቅ ሕዝቡ፥ የሰናዖር ሜዳማ ክፍል ወደ ሆነው ወደ ምሥራቅ ተጓዙ። ሰናዖር በእስራኤል ታሪክ ውስጥ አስፈላጊ የሆነችው የባቢሎን ከተማ ሌላ መጠሪያ በመሆኗ ነው።

ወደ ባቢሎን ሜዳማ ሥፍራ በደረሱ ጊዜ፥ ሕዝቡ ከተማና ግንብ ለመሥራት ወሰኑ። ከተማና ግንብ ለመሥራት የፈለጉባቸው ሁለት ምክንያቶች ነበሩ። በመጀመሪያ፥ ዝነኞች ለመሆን ፈለጉ። ከትዕቢት የተነሣ፥ በሥራቸው፥ በከተማቸውና በግንባቸው ሰው ሁሉ እንዲደነቅና በዚህም ምክንያት የተከበሩ ሰዎች ሆነው ለመኖር ፈለጉ።

15ኛ ጥያቄ፤ - ዛሬ አንዳንድ ሰዎች እንደ እነዚህ የሚሆኑት እንዴት ነው?

ሁለተኛ፥ ሰው በዓለም ሁሉ እንዳይበተን፥ ከተማዪቱን የመሰብሰቢያ ሥፍራ አድርገው ለመጠቀም ፈለጉ። ሰዎች በባቢሎን አካባቢ እንዲኖሩና አንድ ሰፊ መንግሥት እንዲመሠርቱ ወደዱ።

16ኛ ጥያቄ፤ - ይህ እግዚአብሔር ለኖኅ በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ዓመፅ የሚሆነው እንዴት ነው?

ሕዝቡ ከተማና ትልቅ ግንብ መሥራት ጀመሩ። በሰዎቹ መካከል አንድነት ስለ ነበረና በአንድ ልብና በአንድ ዓላማ ስለሚሠሩ፥ ከተማዪቱ በፍጥነት አደገች፤ ግንቡም «እስከ ሰማይ» ደረሰ። ይህ አባባል ግንቡ ወደ ሰማይ ከፍ እንዳለ የሚያመለክት የዕብራውያን አገላለጽ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ሕዝቡ ምን እየሠራ እንዳለ ለማየት እግዚአብሔር እንደ «ወረደ» ይናገራል። እግዚአብሔር ሰው የሚሠራውን ነገር ሁሉ እንደሚያውቅ፥ በሰው ልብ ውስጥ የተሰወሩትንም እንኳ እንደሚረዳ [መዝ. (139)፡1-18]፥ ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እናውቃለን። እናም እግዚአብሔር ወደ ባቢሎን ከተማ የወረደው በዚያ ሥፍራ ምን እየተደረገ እንደ ነበረ ስላላወቀ ያለመሆኑ ግልጽ ነው።

ይልቁንም ሙሴ ሁለት ነገሮችን ለማሳየት የተለመደ የሰው የንግግር ዘይቤ እየተጠቀመ ነው። በመጀመሪያ፡ ሙሴ እግዚአብሔር እንዴት በሰው ሥራዎች ውስጥ ቅርብ ጣልቃ-ገብነት እንዳለው ለማሳየት ይፈልጋል። እኛ የምናመልከው እግዚአብሔር የሩቅ አምላክ አይደለም፤ እግዚአብሔር የምናስበውንና የምንሠራውን ሁሉ ያውቃል። ከእርሱ ዓይኖች ፊት የተሰወረ ነገር የለም።

17ኛ ጥያቄ፤ ሀ) አንዳንድ ጊዜ እኛ የምንሠራውን ነገር እንዴት ከእግዚአብሔር እንደተሰወረ አድርገን እንደምናስብ ግለጽ።

ለ) እግዚአብሔር የምናስበውንና የምንሠራውን ሁሉ እንደሚያውቅና እንደሚያይ ብንረዳ፤ ሥራችንን ምን ያህል እንለውጥ ነበር?

ሁለተኛ፤ ሙሴ የሰውን ሞኝነት ለማሳየት የቃላት ጨዋታ ይጠቀማል። የባቢሎን ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ለመድረስ ግንብ እየሠሩ ነበር። ዳሩ ግን ግንባቸውን እስከ ምንም ያህል ከፍታ ቢሠሩ፤ በፍጹም ወደ እግዚአብሔር ዘንድ አይደርሱም። ሁል ጊዜም እግዚአብሔር ወደ እነርሱ መውረድ ነበረበት። ሰው የሚያደርገው ማንኛውም ነገር ወደ እግዚአብሔር እንዲደርስ አይረዳውም። ከዋክብት በቢሊዮን በሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች ከምድር እንደሚርቁ ሁሉ፤ እግዚአብሔርም ከሰው ልጅ ግምት እጅግ የበለጠ ነው። ሰውና እግዚአብሔር እንዲገናኙ ከተፈለገ፤ ሁል ጊዜም እግዚአብሔር ወደ ሰው ደረጃ ዝቅ ብሎ መውረድ አለበት።

18ኛ ጥያቄ፤ - ይህ ሰው በእራሱና በሥራው ስለሚያሳየው ትልቅ የመታበይ ዝንባሌ ምን ሊያስተምረን ይገባል?

እግዚአብሔር በሰዎች ድርጊት ላይ አልሳቀም። በአንድነታቸው ውስጥ ትልቅ ኃይል እንደነበረ ተገነዘበ። በአምሳሉ ስለ ተፈጠሩ፤ ታላላቅ ነገሮችን ለመሥራት ይችሉ ነበር። ዛሬ ከምንመለከታቸው አስደናቂ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አኳያ ይህን ልንመሰክር እንችላለን።

19ኛ ጥያቄ፤ - አስደናቂ የሆኑና የሰውን ልጅ ከፍተኛ የፈጠራ ችሎታ የሚያሳዩ፤ አንዳንድ ዘመናዊ የፈጠራ ውጤቶችን ዘርዝር።

እግዚአብሔር የተቆጣው፥ ሰዎች ከተማ ወይም ግንብ ስለ ሠሩ አልነበረም። እነዚህ ነገሮች በራሳቸው ክፉ አልነበሩም። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ያልወደደው የእነዚህን ነገሮች ዓላማ ነው። በሰው ውስጥ ካለው የኃጢአት ተፈጥሮ የተነሣ፥ ከተማዋ፥ ግንቡና የሰው አንድነት በመጨረሻው ወደ ባሰ ክፋት እንደሚያመራ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር። ዛሬም እንኳ፥ ከቴክኖሎጂ ዕድገት ሳቢያ፥ ሰው የሚሠራው እያንዳንዱ ነገር ክፋትን፥ እንዲሁም በጎ ነገርን ለማከናወን ከፍተኛ ብቃት አለው።

20ኛ ጥያቄ፤ - የቴክኖሎጂ ምጥቀት ክፉ ሥራዎችን ለማከናወን የሰውን ችሎታ እንዴት እንዳሳደገ ግለጽ።

ከተማዪቱንና ግንቡን በህብረት ለመሥራት ያስቻለው የሰው ልጅ አንድነት ስለነበር፥ እግዚአብሔር ያንን አንድነት ለማስወገድ ወሰነ። ውሳኔውንም በከተማዪቱ ግንባታ ሥራ ላይ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ወዲያውኑ የተለያዩ ቋንቋዎችን እንዲናገሩ በማድረግ አጽድቋል። የተለያዩ የቋንቋ ችሎታዎች ከተለያዩ የቤተሰብ ቡድኖች ጋር ግንኙነት ያላቸው ይመስላል። ይሁንና በቋንቋ ለመግባባት ባለመቻላቸው፥ በሰው ልጆች መካከል ክፍፍል ተፈጠረ። በዚህም ዓይነት፥ ሕዝቡ ባቢሎንን ለቀው በዓለም ዙሪያ ሁሉ መበትን ጀመሩ። ይህም መበትን የአዳዲስ ቋንቋዎችን መጀመር ሂደት አጠናከረ። እስከ ዛሬም ድረስ በዓለም ዙሪያ በሺህ የሚቆጠሩ ቋንቋዎች አሉ። አይሁዶች የሰው ልጅ ቋንቋ በዚያ ስለተደባለቀ ሥፍራውን «ባቤል» (ግርግር) ብለውታል። በኋላ ስሙ ባቢሎን ተባለ።

የእግዚአብሔር ፍርድ ሁለት አበይት ውጤቶች ነበሩት፡- በመጀመሪያ፥ ለሕዝቡ ዓመፅና ትዕቢት የተሰጠ ቅጣት ነበር። በቅጣቱም ሕዝቡ ከተምዪቱንና ግንቡን ከመሥራት ታቀቡ። ዛሬ የዓለም ቋንቋዎች የሰው ልጅ በአንድ ላይ ተባብሮ ለመሥራት ባለው ችሎታ ላይ ማዕቀብ ማድረጋቸውን እንደ ቀጠሉ ናቸው። በመሆኑም እግዚአብሔር በሰው ልጅ ላይ ላወረደው ፍርድ ምልክቶች ናቸው።

21ኛ ጥያቄ፤ - ይህ ዛሬ እንዴት እንደሚታይ አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ።

ዳሩ ግን የቋንቋዎች መደባለቅ ለሰው ልጅ ጥበቃም አስፈላጊ ነበር። ክፍፍሎችን በመፍጠር፡ እግዚአብሔር የሰው ልጅ የባሰ ክፋት እንዳያደርግ ገደብ እያበጀለት ነበር። በሰው ልጆች መካከል የሚፈጠረው አንድነት፡ ክፉው የሰው ተፈጥሮ የባሰ የክፋት ሥፍራ እንዲያከናውን ስለሚያደርግ፡ መከፋፈል ለእነዚህ የባሱ ክፋቶች እንደ መግቻ በመሆን ያገለግላል።

22ኛ ጥያቄ፡ - ይህ እንዴት እንደሚሆን አብራራ።

በዚህ ከፍለ-ዘመን ለቴክኖሎጂ ዕድገት ምክንያት ከሆኑት ነገሮች አንዱ የሰው ልጅ በአንድ ቋንቋ ለመግባባት ያደረገው ከፍተኛ ጥረት ነው። በብዙ የዓለም ክፍሎች እንግሊዝኛ የትምህርት ቋንቋ በመሆን ያገለግላል። ይህ በሕክምና ዘዴዎች መስፋፋት፥ በሬድዮና በቴሌቭዥን ግንኙነት፥ ወዘተ. ትልቅ እመርታ ቢያሳይም፥ በሌላ ጎኑ የሰውን ክፋትና ጥፋት የመከወን ብቃት አጎልብቷል (ለምሳሌ የኬሚካል የጦር መሳሪያዎች፥ የኒውክሌር ቦምቦች፥ ወዘተ.)።

ሙሴ በዚህ ታሪክ አማካኝነት ለእስራኤላውያን ሦስት አንኳር ትምህርቶችን ለማስተማር ይፈልጋል። በመጀመሪያ፥ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ላይ የሚያደርገውን የማያቋርጥ ዓመፅ ለማሳየት ይፈልጋል። እግዚአብሔር ኖኅንና ልጆቹን እንዲባዙና ምድርን እንዲሞሉ አዝዞአቸዋል። ሕዝቡ ግን አብረው ለመኖር መፈለጋቸው ከዚህ ትዕዛዝ ጋር በቀጥታ የሚቃረን ነበር። ስለሆነም እግዚአብሔር ትዕዛዙን እንዲያሟሉና በዓለም ሁሉ እንዲሠራጩ ለማድረግ ቋንቋቸውን ደበላለቀው። ዛሬ ሰዎች በዓለም ውስጥ በሚገኙ ከፍለ-ዓለማት ሁሉ መኖራቸው፥ የዚህን ፍርድ ተፈጻሚነት ያረጋግጣል።

ሁለተኛ፥ ሙሴ የሰውን ትዕቢት ከንቱነት ለማሳየት ይፈልጋል። በጥንቱ ዓለም በጥበባቸው የሚታበዩ ሁለት መንግሥታት ነበሩ። በሙሴ ዘመን የእስራኤል ሕዝብ ያደገባት ግብፅ፥ በሥልጣኔ የመጠቀች ነበረች። ግብፃውያን በከፍተኛ ትምህርታቸው፥ በትላልቅ ሕንፃዎቻቸው፥ ወዘተ. በጣም ይታበዩ ነበር። ዛሬም እንኳ በሙሴ ዘመን የታነጹ የግብፅ ሐውልቶች (ፒራሚዶች) የሰውን ልጅ እያስደነቁ

ናቸው። በስተ-ምሥራቅ ደግሞ የባቢሎን ከተማ ነበረች። እርስዋም ዓይን የሚማርክ ውበትና ትላልቅ ሐውልቶች የነበሩባት አስደናቂ ከተማ ነበረች። በከተማዪቱ ውስጥ ታላላቅ ግንቦች ነበሩ። ከግንቦቹም መካከል አንዳንዶቹ ከጠላት ለመከላከል፥ ሌሎች ደግሞ ለሃይማኖታዊ አምልኮ ያገልግሉ ነበር። አንዳንዶቹ ከ90 ሜትር በላይ ከፍታ ነበራቸው። የሰው ልጅ እነዚህን በሰው ጥበብ የተሠሩ ትላልቅ ሐውልቶች ወደ ማክበሩ ያዘነብላል። ይህም የጥንቱ ሰዎች ለራሳቸው ዝና ለማትረፍ እንደፈለጉ ሁሉ፥ ወደ ሰብዓዊ ትዕቢት ይመራል። ዳሩ ግን ትዕቢት በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ክፋት ነው። ታላላቅ ሕዝቦች እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ለረኽም ዘመን ሊኖሩ አልቻሉም። ሙሴ አዲሶቹን የእስራኤል ሕዝብ በራሳቸው፥ ወይም በችሎታቸው እንዳይታበዩ ለማስጠንቀቅ ይፈልጋል። ትዕቢታቸው ወደ አለመታዘዝ ከመራቸው፥ እነርሱም እንደሚቀጡና በአሕዛብ መካከል እንደሚበተኑ እግዚአብሔር ተናግሯል (ዘዳ. 31፡19-22 ተመልከት)። ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመገዛትና ለእርሱም በመታዘዝ ብቻ ነበር የበረከት ዝናብ የሚጎበኛቸው። የሚያሳዝነው ግን እስራኤል ትዕቢተኛና የማትታዘዝ ሆነች። ትዕቢትና በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ አይሁዶች በዓለም ሕዝቦች መካከል እንዲበተኑ አደረገ። እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ያዋርዳል፤ እንዲሁም በአራሳቸው ጉልበት ሳይሆን በእርሱ ላይ የሚደገፉትን ትሑታን ከፍ ከፍ ያደርጋል።

23ኛ ጥያቄ፤ - ዛሬ ይህ ለእኛ አስፈላጊ እውነት የሚሆነው ለምንድነው? (ሉቃ. 14፡11 ተመልከት)።

ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፥ ዛሬ ይህ ለእኛ በጣም አስፈላጊ ማስጠንቀቂያ ነው። እግዚአብሔር ሲባርከንና ብዙዎች ክርስቶስን ሲቀበሉ አብያተ ክርስቲያኖቻችን ያድጋሉ። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር በጣም የተጠቀመባቸው መሪዎች በችሎታቸው ይታበያሉ። ወይም በጣም እስኪስፋፉ ድረስ ያደጉት አብያተ ክርስቲያናት በእምነት አቋማቸው ይታበያሉ። ይህም ትዕቢት ወደ እግዚአብሔር ፍርድ ይመራል።

24ኛ ጥያቄ፤ - በክርስቲያን መሪዎች ሕይወት፥ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን የእምነት ክፍፍሎች (ዲኖሚኔሽንስ) ዘንድ፥

ብዙውን ጊዜ ስኬታማነት ወደ ትዕቢት የሚመራው እንዴት ነው?

የዛሬ መንግሥታትም ከእዚህ መማር ያስፈልጋቸዋል። የቀደሙት ታላላቅ መንግሥታት እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ዝቅ እንደሚያደርግ ምስክሮች ናቸው። እንደ ግብፅ፥ አሦር፥ ባቢሎን፥ ግሪክ፥ ሮም፥ ወዘተ. ያሉ የቀደሙት መንግሥታት ሁሉ ኃይላቸውን አጥተዋል። በቅርብ ታሪክም እግዚአብሔር እንደ እንግሊዝ፥ ጀርመን፥ ሶቭየት ህብረት፥ ወዘተ. የመሳለሉትን አገሮች ትዕቢት ሲያዋርድ አይተናል። ማንኛውም ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ሳይሰጥ፥ በስኬታማነቱ የሚታበይ ሕዝብ፥ ፍጻሜው ውድቀትና በእግዚአብሔር መደምሰስ ነው።

ባቢሎን ራሳቸውን በትዕቢት ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ከተሞች፥ አገሮች፥ ወይም ሕዝቦች ሁሉ ምሳሌ ነች። ዛሬ በዙሪያችን ዘመናዊ ባቢሎኖች ሞልተዋል፤ እግዚአብሔር ግን አንድ ቀን ያጠፋቸዋል። በሰው ሥራዎች ከመደነቅ ወይም በእግዚአብሔር ላይ ከሚፈጸም ክፉ ዓመፅ ከመካፈል ልንጠነቀቅ ይገባል። ድሉ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ነው። እርሱ አንድ ቀን ሰዎችና አገሮች ሁሉ እንደሚዋረዱ ቃል ገብቷል። ሁላቸውም እውነተኛው የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ በሆነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ይሰግዳሉ። እራሳቸውን የሚያዋርዱና እምነታቸውን በሰው ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ የሚጥሉ ይከብራሉ። ከክርስቶስም ጋር ለዘላለም ይነግሣሉ (ራእይ 20፡6)።

ሦስተኛ፥ ሙሴ ለእስራኤላውያን የባዕድ አምልኮን ከንቱነት ለማሳየት ይፈልጋል። በጥንት ጊዜ ባቢሎናውያን ግንቦችን ከሚሠሩባቸው አበይት ምክንያቶች አንዱ ለሃይማኖታዊ አምልኮ ነበር። በእርግጥ ባቢሎናውያን የባቢሎንን ከተማና ታላላቅ ግንቦች የማነጽ ተመሳሳይ ታሪክ ነበራቸው። ከተማን የሚሠሩት አማልክት እንደሆኑና በግንቦቹም ጫፍ ላይ እንደሚኖሩ ይናገሩ ነበር። አንዳንድ ምሁራን የባቢሎን ግንብ ከእነዚህ ጥንታዊ የአምልኮ ሐውልቶች አንዱ እንደ ነበረ ያስባሉ። ሙሴ የእነዚህን እምነቶች ከንቱነትና የሕዝብ አማልክት በተባሉት ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለእስራኤላውያን

ለማስተማር ይፈልጋል። የሰውን ልጆች የበተነው፥ የሰዎች ሁሉ አምላክ የሆነው አንዱ እግዚአብሔር ነበር። እርሱ የነገሮች ሁሉ ተቆጣጣሪ ስለሆነ፥ የአሕዛብን አማልክት ያጠፋል።

25ኛ ጥያቄ፤- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት። ኢሳ. 13፡19፤ 47፡1፥ 8-13፤ ራእይ 17-18። በእነዚህ ጥቅሶች ባቢሎን የተገለጸችው እንዴት ነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ፥ ባቢሎን የክፉ ነገር፥ እግዚአብሔርን የማይፈራ ህብረተሰብ ተምሳሌት ሆና ቀርባለች። ሙሴ ዘፍጥረትን ከጻፈ ከብዙ ሺህ ዓመታት በኋላ፥ የይሁዳን ሕዝብ ያጠፋው የባቢሎን ሕዝብ ነበር። ባቢሎን በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ለምትጫወተው ሚና፥ ይህ ታሪክ ትንሽ ፍንጭ ወይንም ትንቢት ይሆንን? ባቢሎን የእግዚአብሔር ጠላቶች ተምሳሌት ነች - ከሰይጣን ጀምሮ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ላይ ጦርነት ለመክፈት በምድር ላይ የሚነሣውን የመጨረሻ መንግሥት የምትወክል ነች። በትዕቢት ከግዚአብሔር ጋር ይዋጋሉ። ዳሩ ግን እነርሱም አንድ ቀን በእግዚአብሔር ይጠፋሉ።

በምድር ላይ አድነትን ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት በሚደረግበት ዘመን ላይ እንገኛለን። ይህ በተባበሩት መንግሥታት ጥረት ውስጥ ተገልጾአል። በአንድ በኩል፥ ሰላምን በምድር ላይ ለማምጣት እገዛ ስለሚያደርግ የማኅበሩ መመሥረት ጥሩ ነው። ዳሩ ግን ለትልቅ ክፋት በር ከፋችም ሊሆን ይችላል። ፈሪሃ-እግዚአብሔር በራቀው መንገድ ዓለምን ቢያስተባብር፥ ትዕቢተኛ ቢሆን፥ በተራው ከእግዚአብሔር ጋር ለመዋጋት መነሣቱ የማይቀር ነው። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ላይሆን ቢችልም እንኳን፥ በዘመን መጨረሻ የዓለም ሕዝቦች ከእግዚአብሔር ጋራ ለመዋጋት እንደሚተባበሩ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያሳያል። ያም ትልቅ ክፋት የሚታይበትና የእግዚአብሔርም ሕዝብ የሚሰደድበት ጊዜ ነው። ታላቁ የፍዳ ዘመን በመባልም ይታወቃል። ይህም ክፉው ዓለም በእግዚአብሔር ፍርድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወደሚጠፋበትና የእግዚአብሔር መንግሥት ወደሚመሠረትበት ጊዜ ያመራል (ራእይ 17-19)። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፥ ሰላምን

በምድር ላይ ለመፍጠር ልንሠራ እንችላለን። ዳሩ ግን ለፀረ-ክርስትና፥ ለፀረ-እግዚአብሔር፥ ሰብዓዊ አመለካከቶች መታለል የለብንም።

26ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) መንግሥታትንና ሃይማኖትን ለማወሃድ በሚደረገው ሙከራ ላይ ክርስቲያን ምን ዓይነት አቋም ሊኖረው ይገባል?

ለ) እንዴትስ መተባበር እንደሚገባንና ከምን መጠንቀቅ እንደሚያስፈልገን ተናገር።

የዓለም ከነገድና ከቋንቋ መሠረቶች አኳያ መከፋፈል ለሰው ልጅ ክፉት ምስክር ነው። ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ከፍፍሎች መቼ እንደሚያበቁ ይተነብያል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ፥ እነዚህ ክፍፍሎች የሚያከትሙባት የመጀመሪያ ሥፍራ ቤተ ክርስቲያን እንደምትሆን እንመለከታለን። ጳውሎስ እንዳለው፥ አሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይሁዶች ወይም አሕዛብ የሚል የተለየ ስም የለም (ገላ. 3፡28 ተመልከት)። ዳሩ ግን በመጨረሻ፥ በዘመናት ፍጻሜ፥ በምድር ላይ አንድነትና ሰላምን ለመፍጠር፥ እግዚአብሔር ማናቸውንም የሕዝብ ክፍፍሎች ያስወግዳል፡- (ሶፎ. 3፡9-11፥ ተመልከት።)

27ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) እነዚህ ክፍፍሎች በኢትዮጵያ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚታዩት እንዴት ነው?

ለ) የእነዚህን ክፍፍሎች መጠን ለመቀነስ፥ ክርስቲያን ምን ማድረግ ይችላል? ይህ ታሪክ በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ወደ አንድ አዲስ ምዕራፍ ሲያመራ እንመለከታለን። ከዘፍጥረት 1-11 ያለው እግዚአብሔር ከዓለም ሕዝቦች ጋር ሲሠራ የሚያሳይ መግለጫ ነው። እግዚአብሔር በተደጋጋሚ ጸጋን አሳይቷል። ዳሩ ግን ሰው በተደጋጋሚ፥ በእግዚአብሔር ላይ ማመፁን ቀጥሎ ነበር። ከእዚህ በኋላ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ሁሉ ጋር ከመሥራት ይልቅ፥ በእርሱ በኩል ዓለሙን ለመድረስ የተለየ ሕዝብ የሚሆንለትን ወገን መጥራት ይጀምራል። ይህም የእስራኤል ሕዝብ ነው።

2. የተመረጠው የሴም የዘር ሐረግ (ዘፍ. 11፡10-26)

በዘፍጥረት 10፡21-29፥ ከሴም ዘር የተገኙትን አንዳንድ እጅግ አስፈላጊ ሕዝቦች ለማሳየት፥ ሙሴ በበርካታዎቹ የሴም ትውልዶች ላይ ያተኩራል። እርግጥ ሙሴ እስከ አሁን ያተኮረው በተመረጠው የአብርሃም የዘር ሐረግ ውስጥ በነበሩት ላይ ሳይሆን፥ በዮቅጣን ትውልዶች ላይ ነበር። በመቀጠል ግን ሙሴ ወደ ሴም ሐረግ በመመለስ፥ የተመረጠው ሐረግ አካል በነበሩት የአብርሃም ቅድመ-አያቶች ላይ በተለይ ያተኩራል። ዓላማውም፥ የጥፋት ውኃውን ዓለም፥ ከዚህ በኋላ የዘፍጥረት መጽሐፍ ታሪክ ማተኮሪያ ከሆነበት የአብርሃም ቤተሰብ ጋር በማያያዝ ለማሳየት ነው።

የሚከተለው በዚሁ ክፍል የተገለጸው የሴም ትውልድ ዝርዝር ነው (ዘፍ. 11፡10-30)

ሴም

አርፋክስድ

አባት

ሳላ

የተጋባው

ዔቦር

ፋሌቅ

ራግው

ሴሮሕ

ናኮር

ታራ

ሥራ-------- አብራም ናኮር ሐራን

ሚልካ ዮስካ ሎጥ

3. የታራ የዘር ሐረግ (ቁ. 27-32)

ዘፍጥረት 12-25 የአይሁዶች አባት በሆነው አብርሃም ላይ በይበልጥ ስለሚያተኩር፥ በዚህ ክፍል ውስጥ የአብርሃምን አባት የታራን የቤተሰብ ሐረግና ሁኔታ ዘርዝረናል።

ከላይ ከተመለከተው ሠንጠረዥ ውስጥ፥ የሚከተሉትን ነገሮች አስተውል፡- በመጀመሪያ፥ አብርሃምና ሦራ በጋብቻ ብቻ ሳይሆን፥ ዝምድናም ነበራቸው። ሦራ ከአብራም እናት ባትወለድም፥ የታራ ልጅ ነበረች። ይህ በጥንት ጊዜ የተለመደ ነበር። በኋላ ግን በሙሴ ሕግ ተከልክሏል (ዘሌ. 18)።

28ኛ ጥያቄ፤- እነዚህ በዘመዳሞች መካከል የሚፈጸሙ ጋብቻዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የተለመዱ ናቸውን? ሰዎች ይህን የሚያደርጉት ለምንድነው?

ናኮርም ደግሞ የወንድሙን የካራን ልጅ አግብቷል።

ታራና ቤተሰቡ በከለዳውያን ዑር ኖረዋል። ከለዳውያን የተሰኘው ስም ለባቢሎናውያን የተሰጠ ሌላ መጠሪያ ነው። ዑር በኤፍራጥስ ወንዝ አካባቢ የሚገኝ በጣም የታወቀ ከተማ ነበር። በሥልጣኔው ይታወቅ ነበር። እንዲሁም ደግሞ የጨረቃ አምላክ በማምለኩ የታወቀ ነበር። ታራና ቤተሰቡ ሁሉ ይህን የጨረቃ አምላክ ሳያመልኩ አይቀሩም። ጣዖታትን ያመልኩ እንደነበር ግን በደንብ እናውቃለን (ኢያሱ 24፡2)። እግዚአብሔር አብርሃምን የመረጠው ከሌሎች የተሻለ ስለነበር ሳይሆን፥ በራሱ ሉዓላዊ ምርጫ ነው።

ታራ አብራምን፥ ሦራንና፥ ሎጥን ይዞ ወደ ካራን ስለ ሄደ፥ ዑርን እንዲለቁ እግዚአብሔር ያቀረበውን ጥሪ የተቀበለ ይመስላል። ወደ ከነዓን በመጓዝ ላይ እንዳሉ፥ ከመድረሳቸው በፊት የመጨረሻ ትልቅ ከተማ በሆነችው በካራን ቆይታ አደረጉ። ምናልባት ታራ የሞተው ወደ ከነዓን እየተጓዘ ሳለ፥ ወይም በካራን ሰፍሮ እዚያው በቆየበት ጊዜ ይሆናል። ካራንም የጨረቃ አምልኮ ማዕከል ነበረች።

ሙሴ በኋላ በአብርሃምና ሣራ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት አንድ ሌላ እውነት አክሏል። ሙሴ «ሦራም መካን ነበረች፤ ልጅ አልነበራትም» ብሏል።

29ኛ ጥያቄ፤- አብርሃምን በመጥራቱ፥ የእግዚአብሔር እጅ ሥራ መጀመሩን እንዴት ያረጋግጥልናል?

አራተኛ ቀን፡- የዘፍጥረት 1-11 ክለሳ

ዘፍጥረት 1-11 የዘፍጥረት መጽሐፍን የመጀመሪያ ክፍል ይዞአል። በተለያዩ ነገሮች ጅማሬ ላይ ያተኩራል።

30ኛ ጥያቄ፤- በዚህ በዘፍጥረት መጽሐፍ የመጀመሪያ 11 ምዕራፎች ውስጥ ጅማሬያቸውን ያገኙትን ነገሮች ዘርዝር።

በዚህ ክፍል ውስጥ ለሚገኙት አበይት ትምህርቶች መሠረት የሚጥሉ አራት አንኳር ክስተቶች አሉ።

1. የዓለም አፈጣጠር (ዘፍ. 1-2)

ሙሴ የዓለምን ጅማሬ እጥር-ምጥን አድርጎ አቅርቧል። የፍጥረትን ታሪክ ከሁለት ገጽታዎች አንጻር ዘግቧል። በመጀመሪያ፥ በዘፍጥረት 1 የዓለምን መፈጠር ባጭሩ አቅርቦአል። በምድር ላይ የሚገኙ ነገሮች ሁሉ በስድስት ቀናት ውስጥ ተፈጥረዋል። ዳሩ ግን ሙሴ የእግዚአብሔር የፍጥረታት ቁንጮ በሆነው በሰው ልጅ ላይ አትኩሮአል። ወንድም ሆነ ሴት፥ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረና በእግዚአብሔር አገዛዝ ሥር በምድር ሁሉ ላይ እንዲገዛ ሆኖ የተፈጠረ ነው።

ሁለተኛ፥ ሙሴ በዘፍጥረት 2፥ የወንድና ሴትን የአፈጣጠር ታሪክ በድጋሚ አውግቷል። ወንዱ የተፈጠረው ከምድር አፈር ሲሆን፥ ሴቷ ደግሞ ከወንዱ ጎን ተፈጥራለች። እንዲሁም ሙሴ የሰው ልጅ የመጀመሪያ መኖሪያ ስለሆነችው ዔድን ገነት በዝርዝር ገልጾአል።

31ኛ ጥያቄ፤- ትምህርት ሁለትን ከልስ።

ሀ) በያንዳንዱ ቀን የተፈጠረውን ነገር ዘርዝር።

ለ) እነዚህ ምዕራፎች ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሰው፥ ስለ ጋብቻ፥ ወዘተ. የሚያስተምሩትን በተመለከተ ያደረግናቸውን አበይት ተዛምዶዎች ዘርዝር።

2. የሰው በኃጢአት መውደቅ (ዘፍ. 3-4)

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን የሚኖሩባትን ውብ ሥፍራ ቢሰጣቸውም፡ መልካምና ክፉ ከምታሳውቀው ዛፍ ፍሬ እንዳይበሉ የተሰጣቸውን አንድ ትዕዛዝ ወዲያውኑ ተላለፉ። በሰይጣን ተፈትነው በመጀመሪያ ሔዋን፥ ከዚያም አዳም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጣሱ። ከዚህም የተነሣ የሰይጣን ተምሳሌት የሆነው ሥጋዊው እባብ፥ ሴቲ፡ ወንዱ፥ እና ተፈጥሮ በሙሉ ተረገሙ። አዳምና ሔዋን ከዔድን ገነት ተባርረው በመውጣት፡ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለማግኘት ከባድ ሥራ ለመሥራት ተገደዱ። በዚህ ጊዜ ለልጆቻቸው ያስተላለፉት የኃጢአት ተፈጥሮ ነበራቸው። ኃጢአት እንደ ሰደድ እሳት በፍጥነት እየተቀጣጠለ መሄዱ ቃየን አቤልን በመግደሉና የቃየን ትውልዶች በክፉ ሥራ መፎከራቸው በግልጽ ታየ። እግዚአብሔር ቃየንን ወደ ጎን በመተው፥ የሴትን ሐረግ የእስራኤል ሕዝብና የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ግንድ አድርጎ መረጠ።

32ኛ ጥያቄ፤ - ትምህርት ሦስትን ከልስ።

ሀ) የሔዋን ፈተና ከእኛ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ለ) የውድቀት ውጤቶች ዛሬ በዓለማችን ላይ የሚታዩት እንዴት ነው?

3. በምድር ላይ የጥፋት ውኃ ፍርድ መምጣት (ዘፍጥረት 5-9)።

ሙሴ ከሴት እስከ ኖኅ ድረስ የተመረጠውን ሐረግ ካሳየ በኋላ (ዘፍ. 5)፥ አትኩሮቱን ሦስተኛው አቢይ ክስተት ላይ ያደርጋል። ይህም አብይ ክስተት የጥፋት ውኃ ነው። አንድ ጻድቅ ሰው ብቻ እስኪቀር ድረስ ዓለሙ ሁሉ በክፉት ተሞልቶ ስለ ነበር፥ እግዚአብሔር የኃጢአትን ዓለም ለማንጻትና የሰውን ልጅ የሚያጠፋ ውኃ ለማምጣት ወሰነ። ኖኅና ቤተሰቡ ብቻ አምልጠዋል። ዳሩ ግን የጥፋት ውኃው በሰው ውስጥ ያለውን ክፉ ተፈጥሮ ለማስወገድ አልቻለም። የጥፋት ውኃው እንደ ተፈጸመ፥ ወዲያውኑ ኖኅ በኃጢአት ወደቀ፤ ልጁ ካምም በኃጢአት ወደቀ። ርግማኑም እንደገና ተጀመረ። ወደፊት የእስራኤልና የእግዚአብሔር ጠላቶች የሚሆኑ ሕዝቦች አባት የሆነው ከነዓን ተፈረደበት።

33ኛ ጥያቄ፤ - ትምህርት አራትን ከልስ።

ሀ) ከዘፍ. 1-11 የኃጢአት ተፈጥሮ ያስከተላቸውን ውጤቶች ዘርዝር።

ለ) የጥፋት ውኃው የደኅንነት ምሳሌ የሚሆነው እንዴት ነው?

4. በባቢሎን ግንብ የሰው ልጆች መበተን (ዘፍ. 10-11)

ከኖኅና ቤተሰቡ ዳግም የተጀመረው የሰው ልጅ፥ በፍጥነት በዓለም ሁሉ ተሰራጨ። ዳሩ ግን አንደ አባታቸው ኖኅና ከእርሱ በፊት እንደነበሩት ሁሉ፥ ሁላቸውም የኃጢአት ተፈጥሮ ነበራቸው። እነርሱም በእግዚአብሔር ላይ ዓመፁ። የክፋት ውጤቶችን ለመገደብ፥ የተለያዩ ቋንቋዎች እንዲናገሩ በማድረግ፥ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በታተነ። ሰው በሚሄድበት ሥፍራ ሁሉ፥ የኃጢአት ተፈጥሮውን ይዞ ስለሚሄድ፥ ሁል ጊዜም ክፉ ነገር በዚያ ይገኝ ነበር።

እንዲሁም ሙሴ ከተለየ ቤተሰብ ጋር አስተዋውቆናል። የኖኅ ልጅ ከሆነው ሴም ጀምሮ፥ በኋላ አብርሃም በመባል ከሚታወቀውና የተመረጡት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ማለትም አይሁዶች አባት ከሆነው አብራም ጋር ያስተዋውቀናል።

አሁን ቀጣዩን አቢይ የዘፍጥረት ክፍል ለማጥናት ተዘጋጅተናል። ከዘፍ 12-50 የአብርሃምን የቤተሰብ ሐረግ እስከ አራት ትውልድ ድረስ ይገልጻል። በሚቀጥለው ሳምንት የአይሁዶችና በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ አባት ስለሆነው አብርሃም ማጥናት እንጀምራለን።

34ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ከአዳም እስከ አብርሃም ድረስ በተመረጠው ሐረግ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ሰዎች ዘርዝር።

ለ) ከእነዚህ ቁልፍ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የምንማራቸው አንዳንድ ትምህርቶች ምንድናቸው?

አምስተኛ ቀን፡ - ለሳምንታዊው ስብሰባ የዚህን ሳምንት ትምህርት በመከለስና የውይይት ጥያቄዎችን በመመልከት ተዘጋጅ።

ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ

2. የጸሎት ጊዜ

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. የውይይት ጊዜ

ሀ) እያንዳንዱ ተማሪ የሦስተኛውን ቀን ትምህርት የቤት ሥራ እንዲያቀርብ አድርግ።

ለ) 1) ሰዎች ሁሉ ከአንድ ሰው የመምጣታቸው እውነታ፥ ከተለያየ ነገድ፥ ዘር፥ ከሌላ ሥፍራ ከመጡት ሰዎች፥ ወይም የተለያየ የኑሮ ደረጃ ካላቸው ወይም አካለ ስንኩላን፥ ወዘተ... ከሆኑት ሰዎች ጋር የሚኖረንን ግንኙነት እንዴት ሊለውጠው ይገባል?

ሐ) በኢትዮጵያና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሳይቀር ጎሰኝነት የሚታየው እንዴት ነው?

3) ቤተ ክርስቲያንህ ጎሰኝነትን ከውስጧና ከኢትዮጵያ ለማስወገድ፥ እንዴት መሥራት ትችላለች?

ሐ. 1. የምትችለውን ያህል የኢትዮጵያ ጎሳዎችን ስም ዘርዝር።

2. በውስጣቸው ጥሩ የክርስቲያን ቤተ ክርሲትያንና በርካታ መሪዎች ያሉባቸው ስንት ናቸው?

3) ቤተ ክርስቲያንህ ወንጌልን ለእነርሱ ለማድረስ ያላት መሻት እንዴት ነው?

4) ቤተ ክርስቲያንህ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ጎሳዎችና ከኢትዮጵያ ውጭም ያሉትን በወንጌል ለመድረስ በበለጠ ለመሥራት የምትችለው እንዴት ነው?

መ. 1) ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሰውን ትልቅ ችሎታ የሚያሳየው እንዴት ነው?

2) የሰው የኃጢአት ተፈጥሮ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ውስጥ የሚታየውስ እንዴት ነው?

ሠ. 1) ክርስቲያን ለዓለም አንድነት በመሥራቱ ረገድ፥ በፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ መስኮች የሚኖረው ሃላፊነት ምንድነው?

2) እዚህ ላይ ልንጠነቀቅበት የሚገቡን አደጋዎች ምንድን ናቸው?

3) በኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶችና የእምነት ክፍሎች አድነት መልካም የሚሆነው እንዴት ነው?

4) አደገኛ የሚሆነውስ?

ረ. በዘፍጥረት ጥናትህ እስከዚህ ድረስ የተማርሃቸው አንዳንድ አበይት ትምህርቶች ምንድናቸው?

5. ጸሎት።

ትምህርት ስድስት

ዘፍጥረት 12-15

የመጀመሪያ ቀን፡- ዘፍ. 12፡1-9

ባለፈው ሳምንት ከአብራም ቤተሰብ ጋር ተዋውቀናል። ሙሴ፥ የአብራም አባት ታራ እንዴት ዑርን ለቅቆ ወደሞተበት ወደ ካራን እንደ ሄደ ተርኮልናል። ዘፍጥረት በአብርሃም ላይ ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ፥ ከ12-25 ድረስ ሕይወቱን ይተርክልናል።

1ኛ ጥያቄ፤- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አብርሃም እንደዚህ አስፈላጊ ሰው የሆነው ለምን ይመስልሃል?

በዓለም ታሪክ ውስጥ የአብርሃምን ያህል አስፈላጊነት ያላቸው ሰዎች ጥቂት ናቸው። የአብርሃምን ታሪክና እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን መረዳታችን፥ ለመጽሐፍ ቅዱስና ለዓለም የወደፊት ዕጣ ለሚኖረን ግንዛቤ መሠረት ነው።

ሦስት አበይት ሃይማኖቶች፥ አብርሃምን የእምነት አባታቸው አድርገው ይቀበላሉ። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር የአይሁድን ሕዝብ ለመመሥረት ቃል ኪዳን የገባው ከአብርሃም ጋር ስለ ነበር፥ አይሁዶች አብርሃምን የመጀመሪያው አይሁድ አድርገው ይመለከታሉ። ሁለተኛ፥ ክርስቲያኖች አብርሃምን ለሚያምኑት ሁሉ የእምነት አባት አድርገው ይመለከቱታል። ሰዎች አብርሃም የነበረው ዓይነት እምነት ከሌላቸው፥ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ሊደባለቁ አይችሉም። ሦስተኛ፥ ሙስሊሞች አብርሃምን እንደ አባታቸው አድርገው በመመልከት፥ እግዚአብሔር የእስማኤልን ትውልዶች እንደሚባርክ ያምናሉ።